# ካፖርቱ

እና

## ሌሎች አጫጭር ታሪኮች

(ትርጉም)

በመስፍን ዓለማየሁ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
፲፱፻፸፰
አዲስ አበባ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kuraz Publishing Agency

ስልክ / TEL. 11 27 19    ፖስታ ሣ.ቍ. / P. O. Box 30933

አዲስ አበባ    ADDIS ABABA
ኢትዮጵያ    ETHIOPIA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
ALL RIGHTS RESERVE

የሽፋን ሥዕል — ስብለ ገብረ ሕይወት

ንግድ ማተሚያ ቤት

መታሰቢያነቷ
ለሻምበል አፈወርቅ ዮሐንስ ይሁን

# ማውጫ


አሮጊቷ ገጽ

ፑሽኪን —— 7

ካፖርቱ ………………………………

ጐጐል —— 39

የማልረሳት ልዩ ወጣት ………………………

ኩሮሊንኮ —— 103

ሴማጋ እንዴት እንደ ተያዘ ………………………

ጐርኪይ —— 144

ኩርኔይ ቫሲሊየቭ ………………………

ቶልስቶይ —— 160

በሽለቆው መኻል ………………………

ቼኮቭ —— 198

# አሌክሳንደር ፑሽኪን

(1799—1837)



በ1799 ተወለደ ። በጊዜው ተራማጅ አስተሳሰብ የነበረው ፑሽኪን፡ ሕይወቱን ለሩሲያ ሥነ ጽሑፍ ዕድገት ያዋለ በመሆኑ ፣ የሀገሪቱ የመጀመሪያዉ የፈጠራ ጽሑፍ ጠቢብለመባል በቅቷል። የፑሽኪንን የሥነ ጽሑፍ ውጤቶች የምዕራባውያን ባለቅኔዎችና የብዕር ሰዎች ተጽዕኖ የዳሰሳቸው ቢሆንም ፣ አርአያና ምሳሌ ለመሆን በበቁት ፣ በቅኔዉ ፣ በተውኔቱ ፣ በልቦለድና አጫጭር ድርሰቶቹ ጥራቀትና ምጥቀት ፣ ብሔራዊ ባለቅኔነቱን ለማስመስከር ችሏል ። ፑሽኪን በሰፊ የሥነ-ግጥምና የስድ ጽሑፍ አዝመራው አማካይነት ዘመናዊዉን ሥነ - ጽሑፋዊ ቋንቋ ለሩሲያ ያበረከተ ታላቅ የፈጠራ ሰው በመሆኑ ፤ ‘ የሩሲያ ሥነ-ጽሑፍ ታላቁ ጴጥሮስ ’ እያሉ የሚጠሩትም አልታጡም ። የዛሬዋ ሶቪዬት ኅብረት ደራሲያንም ፣ ‘ የሕዝባችን ነፍስ ’ የሚል ስያሜ የሰጡት ያለ ምክንያት አይደለም ። የአርበኝነትን ባሕርይ ፣ ጠንካራ ብሔራዊ ኩራትንና ለሩሲያ ዐፈር ያለውን ጥልቅ ፍቅር ከአብዮታዊ ስሜቶች ጋር በማዋሐድ በቅኔዎቹ ይገልጥ ስለ ነበር ነው። ይህም ስለ ሥራውና ስለ ሕይወቱ በሚተርኩ ገድሎች

---

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ዓመተ ምሕረቶች በሙሉ በአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ላይ የተመሠረቱ ናቸው ።

ዴት ብትደፍር ነው ? ጃል ! . . . ለመሆኑ ከማን ፊት እንደ ቆምክ ታውቃለህ ?" በሚል ድንፋታ የበታቾቹን ቀልብ መግፈፉን እርግፍ አድርጎ ተወው ። እንዳጋጣሚ ሆኖ እነ ዚህን ቃላት ቢሰነዝርም እንኳን ፤ በቅድሚያ ሌላው ሰው የሚናገረውን በእንክሮ ከአዳመጠ በኋላ ብቻ ነበር ።

ያ ፡ ኤኬራ የሚፈልገው ነገር የትልቁን ሰው ካፖርት ስለ ነበር ፤ ከዚያ ታሪከኛ ምሽት በኋላ በቅዱስ ፒተር ስቡርግ ከተማ መታየቱን አቆመ ። ለየፖሊስ ጣቢያው ይቀርብ የነበረው የካፖርት ዘረፋ ክስ ወዲያውኑ ተቋረጠ።



# ቪላድሚር ግላክቲዮኖቪች ኮሮሌንኮ

(1853—1921)



በ1852 ሰኔ 27 ቀን ብኡክሬይን ግዛት ፤ ዥቶሚር በምትባል ሥፍራ ተወለደ ። ኮሮሌንኮ ገና የዐሥራ አምስት ዓመት ወጣት ሳለ አባቱ በመሞቱ የተነሣ ፤ በትውልድ አካባቢው ለመኖር አዳጋች ስለ ሆነበት ፤ ትምህርቱን ለመቀጠልና የኑሮውን መሠረት ለመጣል ፤ ወደ ቅዱስ ፒተር ስቡርግ ከተማ አመራ ። ግን በዚያም ሁኔታዎች አመቺና ቀላል አልሆኑለትም ። ከባድ የሕይወት ትግልና ውጣ ውረድ አፋጠጠው ። በተለይም በነጻ አመለካከቱና ለቄሣራዊው የዘውድ አገዛዝ በነበረው የከረረ ጥላቻ ሳቢያ ፤ ከሚማርበት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የመባረርና በኋላም የመጋዝ ዕጣ ገጠመው ። በዚህም መንስኤ በፖለቲካ ፖሊሶች ትኩረትና ጥቁር መዝገብ ውስጥ ገባ ።

በየዳር አገሩ ብዙ የግዞትና የሥቃይ ዘመናትን ካሳለፈ በኋላ ፤ ነጻ ኑሮ ሲጀምር የሥነ ጽሑፍ ሥራውን ተያያዘው። ከአፍላ የወጣትነት ዕድሜው እንሥቶ መጋዝና መንከራተት ከገበሬውና በጠቅላላውም ለትልተኛው ሥርዓት ከተ

